https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 20
ADDIS ABABA 25th, March 2020

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፮/፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ……………………………………………………ገጽ ፲፪ሺ፪፻፴፪

**Content**

Proclamation No. 1176/2020

Prevention and Suppression of Terrorism Crimes Proclamation ……………………………………Page 12232

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፮/፪ሺ፲፪

## የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

የሽብር ድርጊት በሰው ልጆችና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ የሚገኝ ወንጀል ሲሆን፣ ለአገራችንና ለዓለም ህዝብ ሰላምና ደህንነት ከፍተኛ ስጋት መሆኑን በመገንዘብ፣

መንግስት የአገርና የህዝብን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ወንጀሉን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ባህሪውን ያማከለ ጠንካራ ቅድመ ጥንቃቄና ዝግጅት ማድረግ እንዲሁም አጥፊዎች ከድርጊታቸው ጋር ተመጣጣኝና አስተማሪ ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፣

## PROCLAMATION NO. 1176/2020

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PREVENTION AND SUPPRESSION OF TERRORISM CRIMES

**WHEREAS**, act of terrorism is a serious threat to peace and security of our Country and International Community causing serious damage to human and property;

**WHEREAS,** the Government has the responsibility to maintain peace and security of the country; thus to prevent and control the crime, necessitate to adopt Legal Framework that enable to take strong precautionary and preparatory acts centered the nature of the crime as well as ensure perpetrators received penalty proportional to their acts and gives lesson;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me

https://chilot.me



ኢትዮጵያ የሽብር ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የፀረ-ሽብር ዓላማ ካላቸው አገራት ጋር ለመተባበር እና አባል የሆነችባቸውንና የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተለይ በተባበሩት መንግስታትና በአፍሪካ ህብረት የተደረጉት ስምምነቶችንና የተላለፉ ውሳኔዎችን ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊነቱ የታመነበት በመሆኑ፤

የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ወጥቶ የነበረው የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ በይዘትና አፈጻጸም ክፍተቶች የነበሩበት በመሆኑ በዜጎች መብት እና ነጻነት ላይ አሉታዊ ተጽኖ ያሳደረ ሆኖ በመገኘቱ፤ የግለሰቦችን መብቶችና ነፃነቶች በበቂ ሁኔታ ሊያስጠብቅና የህግ አሰፈጻሚ አካላትን ተጠያቂነት ማስፈን በሚያስችል ሕግ መተካት በማስፈለጉ፤

የሽብር ድርጊት ተጎጂዎች የህክምና፣ መልሶ ማቋቋምና መሰል ተግባራት ድጋፍ ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፭) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፮/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**WHEREAS**, Ethiopia to prevent and suppress terrorist acts, it is believed to be necessary to cooperate with countries having Anti-Terrorism as their objectives and to implement International treaties to which Ethiopia is a party and accepted in particular Treaties and resolutions adopted by the United Nations and African Union;

**WHEREAS,** become necessary to replace the Anti-Terrorism Proclamation No. 652/2009, a Proclamation were enacted to prevent and suppress terrorism, has substantive and enforcement loopholes which produced a negative effect on the rights and freedoms of citizens, with a law that enables adequately to protect rights and freedoms of individuals and prevalence of accountability of law enforcement bodies;

**WHEREAS,** it has become necessary to create a system which would enable to provide medical care, rehabilitative and other related support to victims of terrorist acts;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (5) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Prevention and Suppression of Terrorism Crimes Proclamation No.1176/2020".

www.chilot.me

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **“ንብረት”** ማለት ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ፤ ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ማንኛውም ሀብት ነው፤

፪/ **“የሽብር ወንጀል”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫፣ ከአንቀጽ ፭ እስከ አንቀጽ ፲፩፣ አንቀጽ ፳፱ እና ፴ የተመለከቱት ወንጀሎች ናቸው፤

፫/ **“ድርጅት”** ማለት ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ወይም ሁለትና ከሁለት በላይ አባላትን የያዘ ማህበር ወይም የተደራጀ ማንኛውም ቡድን ነው፤

፬/ “**አሸባሪ ድርጅት**” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በአሸባሪነት የተሰየመ ድርጅት ነው፤

፭/ **“ከሽብር ወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረት”** ማለት ለሽብር ወንጀል መፈጸሚያነት የዋለ ንብረት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በወንጀሉ የተገኘው ንብረት፣ ከወንጀሉ በተገኘው ንብረት የተፈራው ንብረት ወይም በእነዚህ ሁኔታ የተገኘው ንብረት ያልተገኘ እንደሆነ ተመጣጣኝ ግምት ያለው የወንጀል ፈጻሚው ንብረትን ያጠቃልላል፤

፮/ **“ማቀድ”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫ ላይ ሽብር ወንጀልን ለመፈጸም ከማሰብ ባለፈ ወንጀሉን የሚፈጽምበት ሁኔታ፣ ቦታ፣ ጊዜ ወይም መሰል ጉዳዮች የመለየት ወይም የመወሰን ተግባር ማከናወን ነው፤

፯/ **“የህዝብ አገልግሎት”** ማለት ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተደራጀ የመሰረተ ልማት ሲሆን እንደ ውኃ ልማት፣ መብራት ኃይል፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን፣ የትራንስፖርት ፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም እነዚህን የመሰሉ ተቋማት ወይም ስርዓቶችን ያካትታል፤

፰/ “**መንግስት**” ማለት የኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት ወይም የክልል አስተዳር ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ **“Property”** means any movable or immovable; corporeal or incorporeal property;

2/**“Terrorism Crime”** means those criminal acts provided under Articles 3, 5 to 11, 29, and 30 of this Proclamation;

3/ **“Organization”** means a juridical person or any group or association consisting of two or more members;

4/ **“Terrorist Organization”** means an Organization proscribed as Terrorist Organization in accordance with this Proclamation:

5/ **“Property Associated with Terrorism Crime”** means property used for committing terrorism crime, direct or indirect proceeds of the crime, property produced from proceeds of the crime, and includes, when the property obtained through these conditions is not found, equivalent property of the offender;

6/ **“Planning”** means to identify or decide the condition, place, time the terrorist act is to be carried out or similar matters beyond the mere intention of committing the crime;

7/ **“Public Service”** means an infrastructure organized to provide service to the public such as water supply, electric power supply, telecommunications and similar other infrastructure, electronics, information communication, information telecommunication, transport, finance or similar other institutions or systems;

8/ **“Government”** means any of those Regional States specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa Cities Administrations;

www.chilot.me

፱/ **"ዓለም አቀፍ ድርጅት"** ማለት ማለት በዓለምአቀፍ ስምምነት አማካኝነት በሀገራት አባልነት የተመሰረት ድርጅት የተባበሩት መንግስታት፤የአፍሪካ ህብረት ፤የአውሮፓ ህብረት እና ተመሳሳይነት ያላቸውን ድርጅቶች የሚመለከት ሲሆን ሆኖም የግል ዓለምአቀፍ ድርጅቶችን አይጨምርም፤

፲/ **"የወንጀል ህግ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር ፬፻፲፬/፲፱፻፺፮ ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ ነው፤

፲፩/ **"ፖሊስ"** ማለት የፌደራል ፖሊስ ወይም ውክልና የተሰጠው የክልል ፖሊስ ነው፡

፲፪/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ድርጅት ነው፤

፲፫/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለሽብር እና ተያያዥ ወንጀሎች

### ፫.የሽብር ድርጊት

፩/ ማንኛውም ሰው የፖለቲካ፣ የሃይማኖት ወይም የርዕዮት ዓለም ዓላማን ለማራመድ በማሰብ ህዝብን ወይም የተወሰነ የህብረተሰብን ክፍል ለማሸበር ወይም መንግስትን፣ የውጭ አገር መንግስትን ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅትን ለማስገደድ፡-

ሀ) በሰው አካል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ፤

ለ) የሰውን ሕይወት ለአደጋ ያጋለጠ፤

ሐ) ሰውን ያገተ ወይም የጠለፈ፤

መ) በንብረት፣ በተፈጥሮ ሐብት ወይም አካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ፤ ወይም

ሠ) የሕዝብ ወይም ማህበራዊ አገልግሎት እንዳይሰጥ በከፍተኛ ሁኔታ ያስተጓጎለ፤እንደሆነ ከአስር ዓመት እስከ አስራ ስምንት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

9/ **"International Organization"** means an Organization established by treaty or other instrument comprising of two or more countries such as the Unite Nations, African Union, European Union or similar Organizations but does not include Private International Organizations;

10/ **"Criminal Code"** means the Criminal Code of the Federal Democratic Republic of Ethiopia proclaimed by Proclamation No. 414/2004;

11/ **" Police** " means Federal Police or Delegated Regional Police;

12/ **"Person"** means a Natural Person or Juridical Person;

13/ Any expression in the Masculine gender includes the Feminine.

## PART TWO

## TERRORISM AND RELATED CRIMES

### 3. Terrorist Acts

1/ Whosoever, with the intention of advancing political, religious or ideological causes for terrorizing, or spreading fear among the public or section of the public or coercing or compelling the Government, Foreign Government or International Organization:

a) Causes serious bodily injury to person;

b) Endangers the life of a person;

c) Commits hostage taking or kidnapping;

d) Causes damage to property, natural resource or environment; or

e) Seriously obstructs public or social service; is punishable with rigorous imprisonment from ten years to eighteen years.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰውን አላማ ለማስፈጸም ፣ የተፈጸመው ተግባር፣ ሰውን መግደል ወይም በታሪካዊ ወይም የባሕል ቅርስ ወይም የመሰረተ ልማት አውታሮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ እንደሆነ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ይቀጣል፡፡

**፬.ልዩ ሁኔታ**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል (ሠ) ቢኖርም የሕዝብ አገልግሎት መስተጓጎል የተከሰተው በህግ ዕውቅና የተሰጠን እንደ የስራ ማቆም አድማ፣ ሰላማዊ ሰልፍ፣ ስብሰባ ወይም መሰል መብት ለመተግበር በሚፈጸም ሂደት ምክንያት እንደሆነ የሽብር ድርጊት ሆኖ አይቆጠርም፡፡

**፭.የሽብር ድርጊት ለመፈጸም መዛት**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ የተመለከተውን የሽብር ድርጊት ለመፈጸም የዛተ ሰው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ዛቻ የሚያስቀጣው የዛተው ሰው አደርገዋለሁ ወይም አስደርገዋለሁ ያለውን ድርጊት ለመፈጸም ያለበት ሁኔታ ወይም ያለው ዕድል ወይም ያደረገው መዛት በህብረተሰቡ ወይም በህብረተሰቡ የተወሰነ ክፍል ላይ የፈጠረውን ወይም ሊፈጥር የሚችለውን ሽብር በማገናዘብ ይሆናል፡፡

**፮. የሽብር ወንጀል ለመፈጸም ማቀድ እና መሰናዳት**

፩/ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫ ላይ የተመለከተውን የሽብር ወንጀል ለመፈጸም የማቀድ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ የተመለከተውን የሽብር ድርጊት ለመፈጸም የመሰናዳት ተግባር የፈፀመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡

2/ Where the action taken to achieve the causes mentioned in Sub-article (1) of this Article is causing death of person or causing serious damage to historical or cultural heritages or infrastructure or property or natural resource environment the punishment shall be rigorous imprisonment from Fifteen years to life or death.

**4. Exception**

Notwithstanding to the provision of Article 3 sub-article (1) (e), obstruction of public service caused by a strike and the obstruction is related to the institution or profession of the strikers or exercising rights recognized by law such as demonstration, assembly and similar rights shall not be deemed to be a terrorist act.

**5. Intimidation to Commit Terrorist Act**

1/ Whosoever intimidates to commit any of the terrorist acts provided for under Article 3 of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment from one year to five years.

2/ Intimidation provided for in Sub-article (1) of this Article shall be punishable by taking into consideration the condition or opportunity under which the intimidator intends to carry out or cause to carry out or the terror that he has created among the public or sections of the public.

**6. Planning and Preparation for Commission of Terrorist Acts**

1/ Whosoever undertakes act of plans to commit any of the terrorist acts provided for under Article 3 of this Proclamation shall be punishable with rigorous imprisonment from three years to seven years.

2/ Whosoever makes preparation to commit any of the terrorist acts provided for under Article 3 of this Proclamation shall be punishable with rigorous imprisonment from five years to twelve years.

**፯. <u>የሽብር ወንጀል ለመፈጸም ማደም</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ የተመለከተውን የሽብር ወንጀል ለመፈጸም ወይም እንዲፈጸም ለማድረግ ያደመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**፰. <u>በሽብር ድርጊት በሐሰት ስለማስፈራራት</u>**

ማንኛውም ሰው ሐሰተኛ መሆኑን እያወቀ የሽብር ድርጊት እንደተፈጸመ ወይም እየተፈጸመ እንደሆነ ወይም እንደሚፈጸም በማንኛውም መንገድ በመግለጽ ወይም የሀሰት ድርጊት በመፈጸም በህዝብ ወይም በህብረተሰብ ወይም በተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ድንጋጤን፣ ሽብርን፣ መረበሽን ወይም ስጋትን የፈጠረ እንደሆነ በቀላል እስራት ወይም ነገሩ ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**፱.<u>ድጋፍ ማድረግ</u>**

፩.ማንኛውም ሰው የሽብር ወንጀል አፈጻጸምን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እያመቻቸ ወይም እየረዳ መሆኑን እያወቀ ወይም ሽብርተኛ ድርጅትን ለመርዳት በማሰብ፡-

ሀ) ሰነድ ወይም መረጃ ያዘጋጀ፣ ያቀረበ ሰጠ፤ ወይም

ለ) የክህሎት፣ የምክር ፣ የሙያ ድጋፍ የሰጠ፤ወይም

ሐ) ማንኛውንም ፈንጂ፣ ድማሚት፣ ተቀጣጣይ ንጥረ-ነገሮችን፣ የጦር መሳሪያ ወይም ሌላ ገዳይነት ያለው መሳሪያ ወይም መርዛማ ንጥረ-ነገሮች፣ ያዘጋጀ፣ ያቀረበ፣ የሰጠ፣ የሸጠ፤ ወይም

መ) ስልጠና የሰጠ ወይም አባላትን የመለመለ፤እንደሆነ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ የተደረገው ድጋፍ የንብረት የሆነ እንደሆነ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ መሰረት ይቀጣል፡፡

**7. <u>Conspiracy to Carry Out Terrorist Acts</u>**

Whosoever commit conspiracy to carry out or cause to carry out terrorist acts provided for under Article 3 of this Proclamation shall be punishable with rigorous imprisonment from five years to twelve years.

**8. <u>False Threat of Terrorist Act</u>**

Whosoever while knowing that it is false, causes shock, fear, anxiety, or worry in the public or in the society or certain section of the society by expressing through any means or performing false act that a terrorist act has been or is being or will be committed shall be punishable with simple imprisonment or if the act caused damage rigorous imprisonment from three years to ten years.

**9. <u>Rendering Support</u>**

1/ Whosoever knowingly supports or assists directly or indirectly the commission of a terrorist act or with the intent to support a terrorist Organization:

a) Prepares, provides or hands over documents or information;

b) Provides technical, counseling or professional support;

c) Prepares, makes available, provides, or sales any explosive, dynamite, inflammable substances, firearms or other lethal weapons or poisonous substances; or

d) Provides training or recruits members;is punishable with rigorous imprisonment from seven years to fifteen years.

2/ Where the support is of a property nature, the Prevention and Control of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013 shall be applicable.

www.chilot.me

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) ወይም (፪) የተመለከተውን ተግባር የፈጸመ ሰው ዋናው የሽብር ወንጀል ባይፈጸምም ወይም ድጋፍ ማድረጉ ተለይቶ ለታወቀ አንድ የሽብር ወንጀል ለመፈጸም ከሚደረግ ዝግጅት ጋር ወይም የሽብር ወንጀሉን ከሚፈጽመው ሰው ጋር ግንኙነት ባይኖረውም ለሽብር ወንጀል ድጋፍ ማድረግ ሆኖ ይቀጣል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኝነት እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል፡፡

፭) በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ ፩ እስከ ፬ የተደነገገው ቢኖርም በሰብአዊ ተግባር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚያደርጉት ሰብአዊ እርዳታ ወይም ሌላውን ሰው የመርዳት የህግ ኃላፊነት ያለበት ሰው ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት ብቻ የሚያደርገው ድጋፍ አያስቀጣም፡፡

## ፲. ማነሳሳት

፩/ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ሌላውን ሰው በመጎትጎት፣ ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ መሰል ዘዴ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫ ላይ የተመለከተውን ወንጀል እንዲፈጽም ያነሳሳ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመ ወይም የተሞከረ እንደሆነ ለወንጀል በተቀመጠው ቅጣት ይቀጣል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫ ላይ የተመለከተ ወንጀል እንዲፈጸም ለማድረግ በንግግር፣ በጽሑፍ፣ በስዕል ወይም በሌላ ማንኛውም አድራጎት በግልጽ ሁኔታ ቅስቀሳ ያደረገ፣ ወይም እንደዚህ ዓይነት ይዘት ያለው ነገር መሆኑን እያወቀ ያተመ፣ ያሳተመ፣ ያስተላለፈ፣ ያሰራጨ፣ ያከማቸ፣ የሸጠ፣ ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ለህዝብ ተደራሽ ያደረገ እና ወንጀሉ የተፈጸመ ወይም የተሞከረ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

3/ A person who commits the acts provided for under Sub Article (1) or (2) of this Article shall be punished with rendering supports though the principal offence was not committed or the support has no relationship with the preparation of the specific terrorist act or with the offender.

4/ Where the acts provided for under Sub-article (1) of this Article are committed by negligence, the punishment shall be simple imprisonment from one year to five years.

5/ Notwithstanding to Sub Article 1 to 4 of this Article a humanitarian aid given by Organizations engaged in humanitarian activities or a support made by a person who has legal duty to support other is not punishable for the support made only to undertake function and duty.

## 10. Incitement

1/ Whosoever to cause the commission of one of the crimes provided for in Article 3 of this Proclamation, intentionally incites another person by inducing, promises, money, gift, threat or any other similar means shall be punishable with a punishment provided for the offence provided that the crime was attempted or committed

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, whosoever in clear manner incites by statement, writing, using image or by any other conduct to cause the commission of any of the acts provided for under Article 3 of this Proclamation or publish, produce, communicate, distribute, store, sell, or make available to the public through any means anything with substance of such kind shall be punishable with rigorous imprisonment from three year to seven years, provided that the crime was attempted or committed.

https://chilot.me



፫/ የወንጀል ህጉ አንቀጽ ፴፮ (፪) ቢኖርም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞ፣ እንዲፈጸም የተፈለገው የሽብር ወንጀል ያልተሞከረ ወይም ያልተፈጸመ እንደሆነ በንኡስ አንቀጾቹ የተመለከቱትን ድርጊቶች የፈጸመ ሰው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

3/ Notwithstanding the provision of Sub-article (2) of Article 36 of the Criminal Code, where the act mentioned has been committed as provided for in Sub-article (1) or (2) of this Article but the intended crime has not materialized or attempted, the person who commits the acts mentioned in the sub-articles shall be punished with rigorous imprisonment from one year to five years.

## ፲፩. ከሽብር ወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረትን ስለመያዝ

፩/ ከሽብር ወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረት መሆኑን እያወቀ ንብረቱን ይዞ የተገኘ ወይም የተገለገለበት ማንኛውም ሰዉ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ድርጊት የተፈጸመው በቸልተኝነት እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

## 11. Possessing Property Associated with Terrorism Crime

1/ Whosoever, knowing that the property is associated with terrorism crime, is found in possession of such property or makes use of it shall, without prejudice to the confiscation of the property, be punishable with rigorous imprisonment from three years to ten years.

2/ Where the act provided under sub-article (1) of this article is committed by negligence, the punishment shall be rigorous imprisonment from one year to three years.

## ፲፪. በጠቋሚ እና በምስክር ላይ የሚፈጸም ወንጀል

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል ጠቋሚ ወይም ምስክር ሊሆን የሚችል ወይም ማስረጃ ያለው ሰው፤ መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለፍትሕ አካላት እንዳይሰጥ ወይም በምርመራ ወይም በክርክር ሂደት ምስክር ሆኖ እንዳይቀርብ በእርሱ ወይም ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የተንኮል፣ የኃይል ስራ፣ የማስፈራራት፣ የማይገባ ጥቅም በመስጠት ወይም በመደለል፣ ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ጣልቃ በመግባት የከለከለ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተመለከተ ወንጀልን አስመልክቶ ጥቆማ ወይም መረጃ የሰጠን፣ ወይም ምስክር ሆነ የቀረበን ሰው መረጃ በመስጠቱ ወይም ምስክር ሆኖ በመቅረቡ ምክንያት፤ በእርሱ ላይ ወይም ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ ጥቃት፣

## 12. Crimes Committed Against Whistleblowers and Witnesses

1/ Whosoever interferes to prevent a person who may be whistleblower or witness or who has evidence of crime provided under this proclamation from giving information or evidence to justice authorities or being a witness in an investigation or judicial proceeding by using sabotage, violence, threat or by extending undue advantage, by inducements or getting involved in any other way against such person or a person who has close relationship with him shall be punished with rigorous imprisonment from three years to seven years.

2/ Whosoever assaults, threats, suppresses or harms any person or a person who has close relationship with such person, who gave information or evidence to justice authorities or appeared as witness in an investigation or judicial proceeding of crime

www.chilot.me

ማስፈራራት፣ ወይም ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ወንጀል በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የጤና ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ፣ እነዚህን ወንጀሎች በሚመለከት አግባብነት ያላቸው ህጎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፲፫.በዳኝነት እና ህግ አስፈጻሚ አካላት ላይ ስለሚፈጸም ወንጀል**

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል መከላከል፣ ምርመራ፣ ክስ ወይም የዳኝነት ስራ የሚሰራ ሰው የስራ ግዴታው የሆነውን ተግባር እንዳያከናውን በዛቻ፣ በማስገደድ ወይም በኃይል ድርጊት ያሰናከለ ወይም ይህን ግዴታውን እንዳያከናውን ወይም ማድረግ የሌለበትን እንዲያደርግ ያደረገ ወይም ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የዛቻ፣ የኃይል ድርጊት ወይም በማንኛውም የማስገደጃ መንገድ በመጠቀም ተግባሩን ያሰናከለ ወይም የማስገደድ ተግባር የፈጸመ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል የመከላከል፣ የምርመራ፣ የክስ ወይም የዳኝነት ስራ የሚሰራ ሰውን በስራው የሚረዳውን ሰው የደበደበ፣ ያስፈራራ ወይም የኃይል ድርጊት የፈጸመበት እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከተው ወንጀል በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የጤና ጉዳትን ወይም ሞትን አስከትሎ እንደሆነ፣ እነዚህን ወንጀሎች በሚመለከት አግባብነት ያላቸው ህጎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

provided for in this Proclamation shall be punishable with rigorous imprisonment from three years to seven years.

3/ Where the crime mentioned in Sub-article (1) or (2) of this Article entailed grave harm to the body or health of the victim or his death, the relevant laws related to these crimes shall apply concurrently.

**13. Crimes Committed Against the Judiciary and Executive Organs**

1/ Whosoever obstructs the functions of a person who is engaged in the prevention, investigation, prosecution or judicial proceeding proper to his office concerning crimes provided for in this Proclamation or prevents him from carrying out his duties by using intimidation, coercion, violence or any other means of intimidation against him or a person who has close relationship with him or causing the performance or omission of an act in violation of his duty, shall be punishable with rigorous imprisonment from three years to seven years.

2/ Whosoever causes bodily injury, threatens or use violence against an individual who assists a person engaged in the prevention, investigation, prosecution or judicial proceedings of crime provided under this Proclamation shall be punishable with rigorous imprisonment from three years to seven years.

3/ Where the crimes provided for under Sub-article (1) and (2) of this Article entailed grave harm to the body or health of the victim or his death, the relevant laws related to these crimes shall apply concurrently.

## ፲፬. ማስረጃ በማጥፋት ስለሚፈጸም ወንጀል

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል በምርመራ ወይም በፍርድ ክርክር ሂደት ላይ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ማስረጃን ያጠፋ፣ ያበላሸ ወይም የደበቀ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ተግባር አፈጻጸም ከባድ በሆነ ጊዜ ወይም ማስረጃው የሽብር ወንጀል ምርመራ ወይም ክርክር ሂደት ውስጥ እንደ ዋና ማስረጃ ሊታይ የሚችልና ወንጀሉን ለማስረዳት የሚውል ዓይነት ሲሆን ቅጣቱ ከሶስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

## ፲፭. አለማስታወቅ እና ተጠርጣሪን መርዳት

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫፣ ፮፣ ፯፣ ፱፣ ፲ እና ፲፩ ከተመለከቱ የሽብር ወንጀሎች ውስጥ አንዱ ሊፈጸም፣ እየተፈጸመ ወይም የተፈጸመ መሆኑን እያወቀ ወይም የወንጀል ፈጻሚውን ማንነት እያወቀ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ወዲያውኑ ለፖሊስ ወይም አግባብ ላለው ህግ አስፈጻሚ አካል ያላስታወቀ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ወንጀልን አለማስታወቁ ከባድ ሲሆን በተለይም መረጃው ቀድሞ ደርሶ ቢሆን የወንጀሉን መፈጸም መከላከል ወይም መቆጣጠር የሚቻል ዓይነት ሲሆን ቅጣቱ ከሶስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው እያወቀ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ወንጀሎች በአንዱ የተጠረጠረን ወይም የተከሰሰን ሰው አስቀድሞ በማስጠንቀቅም ሆነ በመደበቅ፣ ዱካውን በመሸሸግ ወይም በማጥፋት፣ የሚደረግ ምርመራን በማሳሳት ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ተከሶ እንዳይቀርብ የረዳ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

## 14. Crimes Commited By Destroying Evidence

1/ Whosoever destroys, damage, or hide any evidence to be used in the course of investigation or judicial proceedings of crime provided under this proclamation shall be punishable with one year to three years rigorous imprisonment.

2/ Where the acts provided for under Sub-article (1) of this Article committed in grave manner or where the evidence considered as substantial in the investigation or judicial proceeding of terrorism crime and to be used to prove such crime, the punishment shall be rigorous imprisonment from three years to ten years.

## 15. Failure to Notify and Aiding a Suspect

1/ Whosoever without justifiable cause fails to immediately notify to the police or appropriate law enforcement organ knowing that any act provided for in Articles 3, 6, 7, 9 to 10 of this Proclamation is about to be committed, being committed or committed or the identity of the suspect shall be punishable with rigorous imprisonment from one year to three years.

2/ Where the failure to notify is grave and in particular where the notification made in advance could have prevented or contained the commission of the crime, the punishment shall be rigorous imprisonment from three years to seven years.

3/ Whosoever knowingly saves from prosecution, a person who is suspected or accused of committing one of the crimes provided for under Sub-article (1) of this Article whether by warning him or hiding him, by concealing or destroying the traces, by misleading the investigation, or in any other way, shall be punished with rigorous imprisonment from three years to five years.

www.chilot.me

፬) ወንጀሉን መከላከል ወይም ምርመራ በአግባቡ ተከናውኖ ማስቀጣት የተቻለ ወይም ተጠርጣሪን መያዝ የተቻለ ቢሆንም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩ ፣ (፪) እና (፫) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፭) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ግዴታ በህግ ምስጢር ያለመግለጽ መብት ያላቸው ወይም ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ ሆኖም ወንጀሉ ሊፈጸም ወይም እየተፈጸመ ስለመሆኑ መረጃ ያለው ሰው ይህንን መብት ወይም ግዴታ እንደመከላከያ ለማቅረብ አይችልም፡፡

## ፲፮. ስለምስክሮች ጥበቃ

፩/ ማንኛውም ሰው የሽብር ወንጀልን በሚመለከት ጠቋሚ ወይም ምስክር በመሆኑ ምክንያት የእርሱ ወይም የቤተሰቡ ህይወት፣ አካል ወይም ንብረት ለአደጋ የተጋለጠ እንደሆነ በወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፱/፪ሺ፫ መሰረት ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

ሀ) ክሱ የሚሰማበትን ቦታ መቀየር፣

ለ) በፍርድ ቤቱ እየተካሔዱ ያሉ የክስ መስማት ሂደቶች በከፊልም ሆነ በሙሉ እንዳይታተሙ ወይም በማናቸውም መንገድ እንዳይገለጹ መወሰን፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተሰጠን ትዕዛዝ የተላለፈ እንደሆነ በቀላል እስራት ይቀጣል፡፡ ሆኖም ድርጊቱ በክርክሩ አካሄድ ላይ እንቅፋት የፈጠረ ወይም ምስክሩን ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ከሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4/ Notwithstanding the fact that it has been possible to prevent the crime or to cause the punishment of a suspect by successfully carrying out investigation or to arrest the suspect the provisions of (1), (2) and (3) of this Article shall be applicable.

5/ Sub-article (1) of this Article shall not be applicable to a person who has a legal right or obligation not to disclose confidential information. Provided, however, a person who has the information that a crime is about to be committed or is being committed shall not raise such right or obligation as a defense.

## 16. Witness protection

1) Where the life, wellbeing of property of any person or his family is endangered for being a witness or whistleblower of terrorist crimes, he shall be given protection in accordance with the Protection of Witnesses and Whistleblowers of Criminal Offences Proclamation No.699/2010.

2) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the court hearing the case may take the following measures:

a) Change the Venue;

b) Cause not to publish or record the court proceedings in part or in whole or to be released in any form.

3) Whosoever contravenes the order made in accordance with Sub-article (2) of this Article shall be punished with simple imprisonment; where the act hinders the judicial proceedings or endangers the witness, the punishment shall be rigorous imprisonment from one year to seven years and with fine not exceeding Birr fifty thousands.

**፲፯. የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተካፋይነት**

፩/ የወንጀል ሕግ አንቀጽ ፺ (፩) ፣ (፫) እና (፬) ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ የተደነገገው ወንጀል የተፈፀመው የሕግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት እንደሆነ ለወንጀሉ የሚጣለው ቅጣት፡-

ሀ)በቀላል እስራት ወይም እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሆነ ከአንድ መቶ ሺህ ብር እስከ ሁለት መቶ ሺህ ብር፤

ለ) ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሆነ ከሁለት መቶ ሺህ ብር እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር፤

ሐ) ከአስር ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሆነ ከአምስት መቶ ሺህ ብር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር፤

መ) ከሃያ ዓመት በላይ ወይም በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት እንደሆነ ከአንድ ሚሊዮን ብር እስከ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር፤ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ህግ ጠያቂነት ወይም በራሱ አነሳሽነት ድርጅቱ እንዲፈርስ ወይም ንብረቱ እንዲወረስ ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የድርጅቱ መቀጣት የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በየግላቸው ላደረጉት ወንጀል ሊወሰንባቸው የሚገባውን ቅጣት አያስቀርም፡፡

**17. Participation of Juridical Person in the Commission of a Crime**

1/ Notwithstanding Sub-article (1), (3) and (4) of Article 90 of the Criminal Code, where the crime provided for in this Proclamation is committed by a juridical person the punishment shall be:

a) From Birr one hundred thousand to two hundred thousand birr for simple imprisonment or rigorous imprisonment up to five years;

b) From Birr two hundred thousand to five hundred thousand birr for rigorous imprisonment from five to ten years;

c) From Birr five hundred thousand to one million birr for rigorous imprisonment from ten year to twenty years;

d) From Birr one million to one million five hundred thousand birr for rigorous imprisonment above twenty years or life imprisonment or death;

2/ In addition to the punishment provided for in sub-article (1) of this Article, the court may order the dissolution of the juridical person or confiscation of its property upon request by the public prosecutor or on its own motion.

3/ The Punishment imposed on the juridical person in accordance with this Article shall not discharge the officials or employees of the juridical person from punishment to be imposed on the individual for the crime committed.

www.chilot.me

## ክፍል ሶስት

## ድርጅትን በአሸባሪነት ስለመሰየም እና በተሰየመ ድርጅት ውስጥ መሳተፍ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ድርጅትን በአሸባሪነት ስለመሰየም

**፲፰.የመሰየም ሥልጣን**

፩/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብር ወንጀል ውስጥ የተሳተፈ ድርጅትን በአሸባሪነት ለመሰየም ይችላል፡፡

፪/ ምክር ቤቱ ድርጅትን በአሸባሪነት ለመሰየም የሚችለው በሁለት ሶስተኛ የአብላጫ ድምጽ ነው፡፡

፫/ ምክር ቤቱ የድርጅትን በፍርድ ቤት በወንጀል መከሰስ ወይም መቀጣት ሳይጠብቅ በአሸባሪነት የመሰየም ተግባሩን ሊያከናውን ይችላል፡፡

**፲፱.ድርጅትን ለማሰየም መኖር ስለሚገባው ሁኔታ**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድን ድርጅት በአሸባሪነት ለመሰየም የሚቻለው ፡-

ሀ)ድርጅቱ የሽብር ወንጀልን ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀስ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) የድርጅቱ የሥራ አመራር ወይም ውሳኔ ሰጭ አካል ወንጀሉን በአሰራርም ሆነ በግልጽ የተቀበለው ወይም አፈጻጸሙን የመራ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) በአሰራር ወይም በአፈጻጸም ወንጀሉ የድርጅቱ መገለጫ ሲሆን ወይም አብዛኛው የድርጅቱ ሠራተኛ ወንጀሉን በሚያውቁት አኳኋን የሚንቀሳቀስ እንደሆነ ነው፡፡

፪/ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት አንድን ድርጅት በአሸባሪነት ሲሰይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔውን በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ በማድረግ ስያሜው በኢትዮጵያ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## PART THREE

## PROSCRIPTION OF ORGANIZATION AS TERRORIST ORGANIZATION AND PARTICIPATION IN A PROSCRIBED ORGANIZATION

### SECTION ONE

### PROSCRIBING AS A TERRORIST ORGANIZATION

**18.Power to Proscribe**

1/ The House of Peoples' Representatives may proscribe an Organization as a Terrorist Organization.

2/ The House shall, by a two-thirds majority vote proscribe a Terrorist Organization.

3/ The House may undertake act of proscribing a Terrorist without requiring prosecution or punishment of an Organization in court of law.

**19. Conditions for Proscribing an Organization**

1/ Without prejudice to Article 17 of this Proclamation, an Organization may be proscribed as a terrorist where:

a) It operates by carrying terrorist crimes as its objective; or

b) The management or the decision making body of the Organization practices or officially accepts the Crime or leads its operation; or

c) The crime defines the Organization through its operation and conduct or most of it employees carry out its activities with knowledge of the Crime.

2/ Where United Nations Security Council proscribes any Organization as Terrorist Organization and the Council of Ministers officially announces the decision through media, such proscription will be enforceable in Ethiopia.

www.chilot.me

**፳.የውሳኔ ሀሳብ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ አንድ ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱን በሚያሟላ ሁኔታ የሽብር ወንጀል መፈጸሙን ወይም እየፈጸመ ስለመሆኑ ሲያምን ድርጅቱ በአሸባሪነት እንዲሰየም የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

፪/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ሲያጸድቀው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት የሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ ድርጅቱ በአሸባሪነት እንዲሰየም የሚያደርጉትን ዝርዝር ሁኔታ መያዝ ይኖርበታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የውሳኔ ሀሳቡ ምስጢራዊ ጉዳዮችን በዝርዝር ላያካትት ይችላል፤ ሆኖም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ መስጠት እንዲችል ምስጢራዊ የሚባሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ጥቅል መረጃ መያዝ አለበት፡፡

፭/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅል መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ለመስጠት የተቸገረ እንደሆነ የምክር ቤቱን አፈጉባኤ ጨምሮ በቀጥታ ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ የተወሰኑ ተወካዮች ምስጢራዊ ጉዳዩን እንዲመለከቱ ሊወስን ይችላል፡፡ የተመረጡት አባላትም ጉዳዩን በምስጢር የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ለምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተገቢነት በመመርመር አግባብ የሚሉትን አስተያየት ያቀርባሉ፡፡

**20.Procedure for Submission of Recommendations**

1/ Where the Federal Attorney General believes that an Organization has committed or is in the act of committing a terrorist crime which fulfills one of the conditions provided for under Sub-article (1) of Article 19 of this Proclamation, it shall submit a recommendation to the Council of Ministers for the proscription of the Organization as a Terrorist Organization.

2/ Where the Council of Ministers approves the recommendation submitted by the Federal Attorney General, it shall refer it to the House of Peoples' Representatives.

3/ Any recommendation to be submitted pursuant to Sub-article (1) and (2) of this Article shall include detailed reasons for the proscription.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-article (3) of this Article, the recommendation may not include confidential matters in detail. Provided however, in order to enable the House of Peoples' Representatives pass a resolution, the recommendation shall include general information about the confidential information.

5/ Where the House of Peoples' Representatives is unable to pass a resolution based on the general information, it may assign, including the Speaker of the House, some members directly elected among the members of the House to look into the details of confidential matters. The selected members shall have the obligation to keep the information confidential and examine the appropriateness of the recommendation and submit their opinion which they think is appropriate.

https://chilot.me


፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት ጉዳዩ ምስጢራዊ ነው የሚባለው የጉዳዩ መገለጽ በሀገር ደህንነት፣ በህዝብ ፀጥታና ሰላም፣ በመረጃ ምንጩ ወይም በውጭ ግንኙነት ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲያምን ነው፡፡

**፳፩.ጥሪ ስለማድረግ እና ውሳኔ ማስተላለፍ**

፩/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድርጅትን በአሸባሪነት እንዲሰየም የውሳኔ ሀሳብ ሲቀርብለት፣ ድርጅቱ አስተያየቱን የሚያቀርብበትን በቂ ጊዜ በመስጠትና የጊዜ ገደብ በመግለጽ አግባብ ባለው መገናኛ ዘዴ ጥሪ ማስተላለፍ አለበት፡፡

፪/ ጥሪ የተላለፈለት ድርጅት አስተያየት ለማቅረብ ሚስጥራዊ ከሚባሉ ጉዳዮች በስተቀር ማስረጃዎችን የማወቅና የማግኘት መብት ያለው ሲሆን፣ የውሳኔ ሀሳቡን ለመቃወም ለምክር ቤቱ ማንኛውንም ማስረጃ ለማቅረብ ይችላል፡፡

፫/ ጥሪ የተደረገለት ድርጅት ጥሪ በተደረገለት ጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበ ወይም ማስረጃውን ያላቀረበ እንደሆነ በሌለበት ወይም ማስረጃ ባላቀረበበት ምክር ቤቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፬/ ምክር ቤቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ፣ ድርጅቱ ያቀረበውን ማስረጃ እና በራሱ አነሳሽነት ያገኛቸውን ማስረጃዎች በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**፳፪.በአሸባሪነት የመሰየም ውጤት**

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት በአሸባሪነት የተሰየመ ድርጅት ስያሜው ተፈጻሚ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች እና እንቅስቃሴዎች ህጋዊ ውጤት አይኖራቸውም፡፡

6/ The information shall be deemed to be confidential as provided for under Sub-article (4) of this Article where the Council of Ministers believes that the releasing of the information will bring damage to the national security, public security and peace, sources of information or Foreign Relations.

**21. Hearing and Passing of Resolution**

1/ Where a recommendation for proscription of an Organization as a Terrorist Organization is submitted to the House of Peoples' Representatives, it shall invite the Organization through the appropriate media providing sufficient time and stating a specific period of time to give its opinion.

2/ The Organization shall have the right to know and access evidence, with the exception of confidential information, and may submit to the House any evidence in objection to the recommendation.

3/ Where the Organization fails to appear or submit its evidence within the specified period of time, the House shall pass a resolution in his absence or without the submission of any evidence.

4/ The House may accept or reject the recommendation by scrutinizing the recommendations presented by the Council of Minister, evidence submitted by the Organization and evidence obtained on its own initiative.

**22. Effects of Proscription**

1/ Any transactions or dealings of an Organization which has been proscribed as Terrorist Oganization in accordance with this proclamation shall be null and void as of the effective date of the proscription.

www.chilot.me

፪/ በአሸባሪነት የተሰየመው ድርጅት ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት የሆነ እንደሆነ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ያልተደረገ እንደሆነ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ድርጅቱ እንዲፈርስ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማመልከት አለበት፡፡

፫/ በአሸባሪነት የተሰየመ ድርጅት ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመንግስት የሚወረስ ይሆናል፡፡ ንብረቱ እንዲወረስ ትዕዛዝ የመስጠት ሂደት ወቅት የሚኖረው ክርክር ድርጅቱ ከመሰየሙ በፊት በቅን ልቦና ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ያደረጉ የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም የተመለከተ ብቻ ይሆናል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሽብር ወንጀል ጋር የተገናኘ ንብረትን ወይም የአሸባሪ ድርጅትን ንብረት ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ንብረቱ የሚወረስ ድርጅትን በሚመለከት የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርአትና የማስረጃ ህግን ጨምሮ ሌሎች ንብረትን ስለመያዝ፣ ስለማገድ ወይም መውረስን የሚመለከቱ ህጎችን መሰረት የሚመራ ይሆናል፡፡

## ፳፫.<u>የድርጅት ስም፣ ምልክት፣ አርማ ወይም አካባቢ ለውጥ መኖር</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት አንድ ድርጅት በአሸባሪነት ተሰይሞ ወይም በመሰየም ሂደት ላይ እያለ ድርጅቱ ስሙን፣ ምልክቱን፣ ዓርማውን፣ አካባቢውን ወይም መሰል ጉዳዮችን ቢቀይር ወይም ከዚህ ድርጅት ተገንጥሎ ወይም ተከፍሎ በመውጣት እናት ድርጅቱን ሽብርተኛ ያሰኘው ወይም ለማሰኘት መሰረት ከሆነው ሁኔታ ወይም አካሄድ ጋር መሰረታዊ ልዩነት ሳይኖረው ሌላ ድርጅት ቢመሰርት እንደ ሌላ ድርጅት ወይም የተለያዩ ድርጅቶች የሚያስቆጥር አይሆንም፡፡

2/ Where the Organization has its own legal personality and has not been dissolved by a court of law pursuant to Sub-article (2) of Article 17 of this Proclamation, the Federal Attorney General shall request the competent court for the dissolution of the Organization.

3/ The asset of the Organization proscribed as a Terrorist Organization shall be confiscated by Government up on a court order. Any civil proceeding with respect to confiscation of assets shall only relate to the interest of third parties who had dealings in good faith with Organization before the proscription of the Organization.

4/ Without prejudice to Sub-article (3) of this Article, the seizure, attachment or confiscation procedure concerning the property associated with terrorism or the asset of the proscribed Terrorist Organization or seizure of asset of an Organization whose asset is to be confiscated pursuant to Sub-article (2) of Article 19 shall be governed by the relevant laws including Anti-Corruption Procedure and Evidence Law.

## 23. <u>Change of Name, Mark, Emblem and Address of the Organization</u>

1/ In accordance with this Proclamation, where an Organization which is proscribed or in the process of proscriptions as terrorist Organization changes its name, mark, emblem, address or related matters or splits or divides itself from the parent Organization and establishes another Organization with no basic difference with the conditions or activity which identifies the parent Organization as Terrorist Organization, shall not be considered as separate Organization or Organizations.

፪/ በዚህ አዋጅ መሰረት በአሸባሪነት ከተሰየመ ወይም በመሰየም ሂደት እያለ ካለ ድርጅት ጋር ሌላ ድርጅት የተዋሃደ ወይም የተቀላቀለ እንደሆነ ለመጀመሪያው ድርጅት የተሰጠው ወይም የሚሰጠው ስያሜ በሁለተኛውም ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፳፬.** **<u>ከስያሜ ስለመሰረዝ</u>**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በአሸባሪነት ተሰይሞ ያለ ድርጅት ስያሜው እንዲሰረዝለት የውሳኔ ሀሳብ ለሚንስትሮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይችላል፤ ምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳቡን ሲቀበለው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

፪/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በመቀበል፤ ከአሸባሪነት ስያሜ ድርጅትን ለመሰረዝ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሰረት አሸባሪ ድርጅትን ከስያሜ ለመሰረዝ የሚቻለው ድርጅቱ የሽብር ወንጀል መፈጸሙን ያቆመ እና በዚህ ዓይነት ድርጊት ውስጥ ሊሳተፍ የማይችል ስለመሆኑ የታወቀ እንደሆነ ነው፡፡

፬/ የተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት በአንድ ድርጅት ላይ ያሳለፈውን የአሸባሪነት ስያሜ ያነሳ እንደሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት የድርጅቱን መሰየም ለህዝብ ይፋ ባደረገበት አግባብ የስያሜውን መነሳትም ይፋ ያደርጋል፡፡

**፳፭.** **<u>ከስያሜ ለማሰረዝ ስለሚኖር ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው በአሸባሪነት ተሰይሞ ያለ ድርጅት ስያሜው እንዲሰረዝለት ለፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ለማመልከት ይችላል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ Where any other Organization make amalgamation or merger with an Organization which is proscribed or in the process of proscriptions, in accordance with this Proclamation, as Terrorist Organization the terrorist proscription shall also apply to the former.

**24. <u>Revocation of Proscription</u>**

1/The Federal Attorney General may submit recommendation to the Council of Ministers for the revocation of proscription of an Organization that is proscribed as a Terrorist Organization. When the Council accepts the recommendation, it shall submit same to the House of Peoples' Representative.

2/ The House of Peoples' Representatives may revoke the proscription of an Organization, when it accepts recommendations submitted by the Council of Ministers.

3/ A proscription shall be revoked provided that the Organization ceases to engage in Terrorist activities and known that it may not engage in such activities.

4/ Where the United Nations Security Council revoked the terrorist proscription against an organization the Council of Ministers shall announce the same, in accordance with Article 19 sub article 2 of this proclamation, in a manner it has announced the proscription of the Terrorist Organization.

**25. <u>Procedure for Revocation of Proscription</u>**

1/ Any one may apply to the Federal Attorney General for revocation of Organization proscribed as a Terrorist Organization.

2/ The Federal Attorney General shall notify to the applicant its decision within sixty days after having examined the application submitted to it pursuant to Sub-article (1) of this Article.

www.chilot.me

፫) የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በተሰጠው አርባ አምስት ቀን ውስጥ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ያልሰጠ እንደሆነ ለሚንስትሮች ምክር ቤት ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡

፬) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት አቤቱታ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ድርጅቱ ከስያሜ ሊሰረዝ የሚገባበትን ምክንያት ከማስረጃ ጋር ማቅረብ አለበት፡፡

፭) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) መሰረት ውሳኔ በተሰጠ በአንድ ዓመት ውስጥ የዚህ ድርጅት የአሸባሪነት ስያሜው እንዲሰረዝለት ለመጠየቅ አይቻልም፡፡

፮) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተገለጸው የማመልከት መብት የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት ከአሸባሪነት ስያሜው እንዲሰረዝ ከማመልከትና ሂደቱን ከመከታተል ውጪ ሌሎች ተግባራትን ከመፈጸም መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

**፳፮.ከስያሜ መሰረዝ ስለሚኖረው ውጤት**

፩/ የድርጅት የአሸባሪነት ስያሜ መሰረዝ፣ ከአሸባሪነት መሰረዙ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ጊዜ በፊት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሰረት የተከናወኑ ተግባራት ላይ ምንም ዓይነት ውጤት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም የተወረሰ ንብረትን እንዲመለስ መጠየቅን ጨምሮ ያደረጋቸው ግንኙነቶች ህጋዊ ሆነው እንዲቆጠሩ ለመጠየቅ አይችልም፡፡

፪/ ስያሜው የተሰረዘለት ድርጅት በህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የነበረ እና ህጋዊ ሰውነቱን መልሶ ለማግኘት የፈለገ እንደሆነ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ድርጅቱ ህጋዊ ሰውነቱን እንዲያገኝ አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፡፡

3/ Any applicant who is aggrieved by the decision or failure of the Federal Attorney General to render its decision within specified period may submit petition to the Council of Ministers against the decision within forty five days as of the date of decision or any time of its failure to render the decision.

4/ Any person who submits an application pursuant to Sub-article (1) of this Article shall provide the reasons with evidence for the revocation of the proscription.

5/ An application for revocation of proscription shall not be requested within one year as of the date of decision given pursuant to Sub-article (2) or (3) of this Article.

6/ Any Person or Organization who have a right to submit an application pursuant to Sub-article (1) for revocation of proscription must refrain from any activity, with the exception of following the proscription process.

**26. Effects of Revocation**

1/ The revocation of proscription of an Organization shall have no effect on activities undertaken pursuant to Article 22 of this Proclamation prior to the effective date of the proscription. Thus, shall not request the legality of its transactions including the return of confiscated property.

2/ Where the Organization whose proscription was revoked is a juridical person and if it desires to reacquire its legal personality, the Federal Attorney General shall cooperate to have the Organization regain its legal personality.

## ፳፯.የወንጀል ተጠያቂነት ስላለመኖሩ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ድርጅትን ለመሰየም በሚደረገው ሂደት ለመሰየም የሚያስችል ምክንያት የሌለ መሆኑን ለማሳየት መረጃ በማቅረቡ ወይም በአሸባሪነት የተሰየመ ድርጅት ስያሜው እንዲሰረዝለት በመጠየቁ ወይም አቤቱታ በማቅረቡ ብቻ በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ፳፰. ውሳኔን ይፋ ስለማድረግ

፩/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድርጅትን በአሸባሪነት ሲሰይም ወይም ከአሸባሪነት ስያሜ ሲሰርዝ፣ ውሳኔውን አገር አቀፍ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ እና ሌላ አግባብነት ባለው የብዙሐን መገናኛ መንገድ ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ምክር ቤቱ ይፋ የሚያደርገው ውሳኔ እንዳስፈላጊነቱ ድርጅቱ ስለተሰየመበት ምክንያት፣ ስያሜው ተፈጻሚ ስለሚሆንበት ሁኔታ እና መሰል ጉዳዮችን መያዝ አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## በአሸባሪነት በተሰየመ ድርጅት ውስጥ ስለመሳተፍ

## ፳፱. አሸባሪ ድርጅትን መምራት

፩/ ማንኛውም ሰው በአሸባሪነት ተሰይሞ ያለን ድርጅት በአጠቃላይ ወይም የድርጅቱን አንድ ክፍል በኃላፊነት የመራ እንደሆነ ድርጅቱን በመምራቱ ብቻ ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም አንድ ሰው ድርጅቱን መርቷል የሚባለው ድርጅቱን አጠቃላይ ወይም የድርጅቱን አንድ ክፍል በበላይነት ማስተዳደር ወይም እቅድ ማውጣትና አፈጻጸሙን መከታተል ኃላፊነት ያለበት ወይም በድርጅቱ ውስጥ ውሳኔ የማሳለፍ ሥልጣን ያለው፣ ወይም በድርጅቱ ደንብ መሰረት አመራር መሆኑ የተረጋገጠ ወይም በመደበኛው ሁኔታ አንድ አመራር ሊያከናውን የሚገባውን ተግባር ያከናወነ እንደሆነ ነው፡፡

## 27. Absence of Criminal Liability

A person shall not be held criminally liable for requesting revocation of proscription or submitting evidence to show absence of reason for proscription or for lodging an application in the process of proscription.

## 28. Public Announcement

1/ The House of Peoples Representatives shall have its decision of proscription or revocation of proscription announces to the public through country wide Gazette and other relevant means of mass media.

2/ A decision announced under sub-article (1) of this Article may state, as may be necessary, the reasons for the proscription, the condition for the implementation of the proscription and related matters.

## SECTION TWO
## PARTICIPATION IN AN ORGANIZATION PROSCRIBED AS TERRORIST ORGANIZATION

## 29. Heading Terrorist Organization

1/ Whosoever heads an Organization proscribed as a Terrorist Organization as a whole or a part there of shall be punished with rigorous imprisonment from seven to fifteen years, for the mere fact of heading the Organization.

2/ For the purposes of Sub-article (1) of this Article, a person shall be deemed to have headed the Organization if he has the responsibility of overseeing the administration of the Organization in whole or in part, or preparing plans and follow up its implementation or has authority to makes decision or whose management position is ascertained by the rules of the Organization or performs acts, which under normal circumstances are performed by a manager.

www.chilot.me

፫/ ድርጅቱ አሸባሪ በሚል ከመሰየሙ በፊት ድርጅቱን ሲመራ የነበረና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድርጅቱ በአሸባሪነት ከተሰየመበት ዕለት በፊት አመራርነቱን የተወ ሰው አሸባሪ ድርጅትን መምራት በሚል ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም ድርጅቱ በአሸባሪነት ከመሰየሙ በፊት አመራርነቱን የተወ ሰው በዚህ አዋጅም ሆነ በሌላ አግባብነት ባለው ህግ የተደነገገ ሌላ የወንጀል ድርጊት የፈጸሞ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፴. አባል መሆን እና መሰልጠን

፩/ ማንኛውም ሰው አሸባሪ ድርጅት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው በድርጅቱ ውስጥ አባል የሆነ ወይም ስልጠና የወሰደ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም አንድ ሰው በአሸባሪ ድርጅት ውስጥ በአባልነት ተሳትፏል የሚባለው ድርጅቱ በአሸባሪነት ተሰይሞ ባለበት ወቅት የድርጅቱ እንቅስቃሴ ውስጥ የተሳተፈ ወይም በድርጅቱ ደንብ ወይም አሰራር አንድ አባል ማድረግ የሚገባውን አስተዋጽዎ ያደረገ ወይም የድርጅቱን ዓላማ እና አሰራር የተቀበለ ወይም የድርጅቱ ዓላማ እውን እንዲሆን በተግባር የተሳተፈ ወይም በራሱ ነጻ ፍቃድ አባል መሆኑን የገለጸ ወይም በመደበኛ ሁኔታ አንድ አባል ሊያከናውን የሚችለውን ወይም የሚገባውን ተግባር ለድርጅቱ ማከናወኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

3/ A person who headed an Organization and has resigned prior to its proscription as a Terrorist Organization by the House of Peoples' Representatives shall not be held liable for heading the Organization. Provided however, he shall be liable for other offences, if any, that he has committed.

4/ Notwithstanding the Provisions of sub article 3 of this Article a person who resigned his leadership position prior to the terrorist proscription of the Organization shall be liable for any other offence which is punishable under this Proclamation or any other relevant law.

## 30. Membership and Training

1/ Whosoever knowing that the Organization is a Terrorist Organization or should have known such fact, joins the Organization as member or took training shall be punished with rigorous imprisonment from one year to five years.

2/ For the purposes of Sub-Article (1) of this Article, a person shall be deemed to have participated as a member where he has participated in the Organization while the Organization is proscribed as a terrorist Organization; makes contribution as a member as per the Organization Rules or Practices or accepts the objective and operation of the Organization or participated in action to realize the objective of the Organization or makes known his membership on his own free will or it is ascertained that he has performed a task for the Organization which under normal circumstance a member is expected or obliged to perform.

www.chilot.me

፫/ ድርጅቱ አሸባሪ በሚል ከመሰየሙ በፊት በድርጅቱ ውስጥ አባል የነበረ ወይም ስልጠና እየወሰደ ያለ ሰው ድርጅቱ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት ከተሰየመበት ዕለት በፊት አባልነቱን ወይም ስልጠናውን የተወ እንደሆነ በአባልነቱ ወይም በመሰልጠኑ ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ሆኖም የፈጸመው ሌላ ወንጀል ያለእንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም ድርጅቱ በአሸባሪነት ከመሰየሙ በፊት አባልነቱን የተወ ወይም ስልጠናውን ያቋረጠ ሰው በዚህ አዋጅም ሆነ በሌላ አግባብነት ባለው ህግ የተደነገገ ሌላ የወንጀል ድርጊት የፈጸሞ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የሽብር ወንጀልን መከላከል

### ፴፩.ድንገተኛ ፍተሻ

፩/ ፖሊሲ በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጄኔራል ወይም በእርሱ በተወከለ የሥራ ኃላፊ ፈቃድ የሽብር ድርጊትን ለመከላከል ድንገተኛ ፍተሻ ማድረግ ይችላል፡፡

፪/ በተደረገ ድንገተኛ ፍተሻ ወቅት የተያዘ ንብረት ወይም ዕቃ ሲኖር ፖሊስ የንብረቱን ወይም የዕቃውን ዝርዝር አዘጋጅቶ በመፈረም፣ ተጠርጣሪው እና ማግኘት ያልተቻለ ካልሆነ በስተቀር ገለልተኛ ሰው እንዲፈርምበት በማድረግ አንዱን ቅጂ ንብረቱ ወይም ዕቃው ለተያዘበት ሰው መስጠት አለበት፡፡

3/ A person who is a member of an Organization or taking training and resigned from such membership or quit such training prior to proscription of the Organization as Terrorist Organization shall not be held responsible for being a member or participating in the training. Provided however, he shall be liable for other offences, if any, that he has committed.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub Article 3 of the Article a person who resigned his membership or quitted such training prior to the terrorist proscription of the Organization shall be liable for any other offence which is punishable under this Proclamation or any other relevant law.

## PART FOUR

## PREVENTION OF CRIME OF TERRORISM

### 31. Surprise Search

1/ Police may exercise its Power of surprise search to prevent terrorism offences upon permission by the Commissioner General of the Federal Police Commission or a person delegated by him.

2/ Where there is a property seized during surprise search, the police officer shall prepare a list of the property or thing by affixing his signature and cause the suspect and, a neutral person, unless impossible to find, counter sign on it and handover one of the copies to the person whose the property or the thing is seized.

www.chilot.me

**፴፪. ለሽብር ጥቃት የተጋለጡ ሰዎችን ስለማዳን**

፩/ ፖሊስ በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ የሽብር ድርጊት የተፈጸመ ወይም እየተፈጸመ ለመሆኑ ወይም ሊፈጸም እንደሚችል ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረው፡-

ሀ) ለሽብር ጥቃቱ የተጋለጡ ወይም ሊጋለጡ የሚችሉ ሰዎችን ከአካባቢው ወደ አንድ ስፍራ እንዲገቡ ወይም ወደ አንድ ስፍራ እንዳይገቡ ወይም ሥፍራውን እንዲለቁ ወይም በተገለለ ቦታ እንዲቆዩ ለማድረግ፣

ለ) በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በግልም ሆነ በመንግስት የህክምና ተቋም አስቸኳይ የህክምና እርዳታ እንዲያገኙ ተቋማቱን ለማዘዝ፣

ሐ) ለአደጋው ምንጭ የሆነው ወይም ሊሆን የሚችለው እቃ እንዲወድም፣ ከነበረበት ቦታ እንዳይነሳ ወይም ወደ ሌላ ቦታ እንዲወሰድ ለማድረግ፣

መ) ሰዎችን ከመመረዝ ለማዳን ተገቢ የሆኑ ትዕዛዞችን እንዲፈጽሙ ለማዘዝ፣

ሠ) የተመረዘው ቤት፣ ህንጻ፣ ድርጅት ወይም ቦታ በቁጥጥር ስር እንዲውል፣ እና

ረ) አደጋውን ወይም መመረዙን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚያስችል አግባብነት ያለውን እርምጃ ለመውሰድ እና እንዲወስድ ለማድረግ፣ይችላል፡፡

፪/ ፖሊስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚፈጽመው ተግባር የጽሁፍ ወይም የቃል ትዕዛዝ በመስጠት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማስገደድ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

**32. Rescuing Persons Exposed to Terrorist Acts**

1/ Where a police officer has sufficient reason to suspect that a crime has been committed or is being committed or is about to be committed in a given place, he may:

a) Cause persons exposed to terrorist acts to move from the scene to a different location or to restrict them from moving to specific place or to leave the scene or to stay in segregated place;

b) Order private or public health Institutions to provide emergency aid to victims injured by the action;

c) Cause the item that is or about to be the source of the incident to be destroyed, not ; to be removed or be moved to another place;

d) Give appropriate order to individuals to take measures to protect themselves from being poisoned;

e) Put under control buildings, residential, business premises or place affected by poisonous substance; and

f) Take or cause to take appropriate measures to prevent the danger or reduce the risk of poisoning;

2/ The order or measures to be taken by police under Sub-article (1) of this Article shall be in writing or by a word of mouth and where necessary may use force.

፫/ ፖሊስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሰጠውን ትዕዛዝ በሚነገር ማስታወቂያ ሊነሳ ወይም ሊራዘም ይችላል፡፡ ሆኖም ትዕዛዙን ለመስጠት ምክንያት የሆነው ጉዳይ እንደተወገደ ወይም በቁጥጥር ስር እንደዋለ ወይም የሰዎቹ ለአደጋው ተጋላጭነት ቀሪ እንደሆነ በተገለለ ቦታ እንዲቆዩ ወይም ወደ አንድ ስፍራ እንዲገቡ የተሰጠው ትዕዛዝ ወዲያውኑ መነሳት አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ መሰረት ፖሊስ የሰጠውን ትእዛዝ የመፈጸምና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፭/ መንግስት እንደ አስፈላጊነቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከሽብር አደጋ ሰውን ለማዳን እቅድ እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡

**፴፫.** **<u>የአከራይ እና በቤቱ የሚያኖር ሰው ኃላፊነት</u>**

፩/ ማንኛውም የቤት፣ የይዞታ፣ የህንጻ፣ የድርጅት፣ የተሽከርካሪ ወይም ተመሳሳይ መገልገያ አከራይ የሆነ ሰው፤ የተከራዩን ስም፣ አድራሻ፣ የስራ ሁኔታ፣ ዜግነት የሚገልጹ ማስረጃችን የኪራይ ግንኙነቱ ከተቋረጠም በኋላ ለሁለት አመታት የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በቤቱ ውስጥ የውጭ ሀገር ዜጋን ሲያኖር በአቅራቢያው ላለ ፖሊስ ጣቢያ ስለሚያኖረው ሰው ማንነት ዝርዝር በግልጽና የፓስፖርቱን ኮፒ በማያያዝ በሰባ ሁለት ሰአት ውስጥ ማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) የተመለከውን ግዴታ የተላለፈ ሰው እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/ The orders given by the police officer pursuant to sub-article of this Article may be lifted or extended by a notice to be announced. Provided however, the order given to keep individuals in segregated place or move to specific place shall be lifted immediately when the reason which gave rise to the issuance of the order is abolished or is under control or the risk of exposure of individuals reduced to nil.

4/ Every person based on this Article shall have the obligation to carry out the order given by a police officer and cooperate.

5/ The Government may, by a Directive order any manufacturing or service rendering institution to have a terrorist act protection plan to protect individuals from the risk of terrorist acts, as may be necessary.

**33. <u>Obligation of a Lessor and Accommodation Provider</u>**

1/ A lessor who rents house, premises, buildings, Organization facilities, vehicles or any other equipment and facilities shall have the responsibility to keep documents relating to name, address, occupation, and Nationality of the lessee until two years after the termination of the lease.

2/ Whosoever provides accommodation to a foreigner in its premise shall submit a copy of the details within in seventy two hours about the identity of the foreigner and the copy of his passport to the nearest police station.

3/ Whosoever contravenes the obligations provided for under Sub-article (1) or (2) of this article shall be punished with simple imprisonment not exceeding one year or with fine from Birr ten five to fifty Thousand.

www.chilot.me

https://chilot.me



**፴፬.መረጃ የመስጠት ግዴታ**

፩/ ፖሊስ የሽብር ወንጀልን ለመከላከል ወይም ምርመራ ለማከናወን የሚረዳዉ መሆኑን በሚገባ የሚያምንበትን መረጃ ወይም ማስረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲሰጠዉ ለመጠየቅና ለመውሰድ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ፖሊስ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥመው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለመጠየቅና ለመውሰድ ይችላል፣ ሆኖም ጉዳዩን በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ለፍርድ ቤት የማሳወቅና ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ትዕዛዝ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ( ፩ ) ወይም ( ፪ ) መሰረት የተገኘው መረጃ ወይም ማስረጃ ምስጢራዊ ይዘት ያለው እንደሆነ፣ ፖሊስ መረጃውን ወይም ማስረጃውን በምስጢር የመያዝ እና ለተፈለገበት ዓላማ ብቻ የማዋል ግዴታ አለበት፡፡

**፴፭. የሽብር አስተሳሰብና ወደ ኃይል የሚያመራ ጽንፈኝነትን ስለመከላከል**

፩/ መንግስት ለሽብር ዓላማ ማንኛውም ሰው በተለይም ህጻናት እና ወጣቶች እንዳይመለመሉ፣ የሽብር ድርጊት አስተሳሰብ ወይም ወደ ኃይል የሚያመራ ጽንፈኝነት እንዳይሰርጽባቸው የማስተማር እና የመከላከል ኃላፊነት አለበት፡፡

፪/ የሽብር ድርጊት አስተሳሰብ ወይም ወደ ኃይል የሚያመራ ጽንፈኝነት እንዲሰርጽባቸው የተደረጉ፣ የሽብር ድርጊት እንዲፈጽሙ የተመለመሉ ወይም በሽብር ድርጊት ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች ሲኖሩ በወንጀል ህጉ የሚፈጸሙ ቅጣቶች እና እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ አስተሳሰብ እንዲወጡ መንግስት መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

**34. Obligation to Provide Information**

1/ A Police officer may request with court order information or evidence which he believes would enable him to prevent crimes of terrorism or carry out investigation from any Government Office, private Organization or Individual.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article a police officer, in urgent case, may request and take information or evidence without court order; provided, however, shall submit the case to the court within seventy two hours and obey order given.

3/ Where information or evidence obtained pursuant to sub-article (1) or (2) of this article has nature of secrecy, the police shall the duty to keep it confidentially and use only for intended purpose.

**35. Prevention of Terrorism Ideas and Extremism**

1/ The Government shall have the responsibility to prevent the recruitment of children and youth for terrorist causes, prevent the inculcation of terrorist ideas or notions of extremism and educate them.

2/ Where there are children and young offenders in whom the idea of terrorism and extremism is inculcated, recruited for the commission of terrorist acts or participated in the commission of such acts, the Government shall, without prejudice to penalties and measures provided for in the Criminal Code, take appropriate measures, in cooperation with non-Governmental Organization, to free them from such ideas.

www.chilot.me

፫/ መንግስት ለሽብር አስተሳሰብ ወይም ወደ ኃይል የሚያመራ ጽንፈኝነት የተጋለጡ ሰዎች ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች ከዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ እንዲወጡ የማስተማር እና አስፈላጊ ሲሆንም የህክምና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡

፬/ የሽብር ወንጀል በመፈጸማቸው በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሆነው በማረሚያ ቤት ለሚገኙ ታራሚዎች የሚሰጠው የማረም ተግባር ከሽብር አስተሳሰብ ወይም ከጽንፈኝነት እንዲወጡ የሚያግዝ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለተቋማት ሚና እና ተጠያቂነት

### ፴፮. የፌደራል ፖሊስ

፩/ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ወንጀሎችን በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሶ ይመረምራል፣ ተጠርጣሪዎችን ይይዛል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የክልል ፖሊስ ተቋምን ትብብር ለመጠየቅ ይችላል፤ የክልል ፖሊስ ተቋምም ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ የሚያከናውኑ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞችን መርጦ ይመድባል፤ የተለየ የሥራ ክፍልም ያደራጃል፡፡

፫/ ምርመራ ለማከናወን የሚመድበው ባለሙያ በሽብር ጉዳይ እና በሰብአዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ስልጠና የወሰደ፣ የሥራ ልምድ፣ ክህሎት እና መልካም ስነ-ምግባር ያለው መሆን አለበት፡፡

፬/ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለክልል ፖሊስ በውክልና ሲሰጥ ውክልና የሚሰጠው የክልል ፖሊስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተውን ሁኔታ በሚያሟላ ባለሙያ ኃላፊነቱን ሊወጣ የሚችል እንዲሁም ውክልናው ከተሰጠው በኋላም ሁኔታውን ባሟላ መልኩ እየፈጸመ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

3/ The Government shall educate persons or sections of a community exposed to ideas of terrorism and extremism to free them from such outlook and ideology and, where necessary, provide them with medical support.

4/ The rehabilitative measure provided in prison for convicted and sentenced prisoners shall be in manner it helps them to be free from extremism.

## PART FIVE

## ROLE AND ACCOUNTABILITY OF INSTITUTIONS

### 36. Federal Police

1/ The Federal Police shall have the Power to investigate crimes provided for in this Proclamation and may seek cooperation from Regional Police Institutions. The Regional Police Institution shall have the obligation to cooperate.

2/ The Federal Police shall select and assign investigators from among its officers and, where necessary, organize a specialized work unit for the purpose.

3/ A professional to be assigned as an investigator shall be a person who has taken training on matters of crimes of terrorism and protection of human rights and who possesses the required experience, skill and good ethical behavior.

4/ Where the Federal Police delegates powers entrusted under this Proclamation to Regional Police, it shall have the responsibility to ensure that the Regional Police carries out the responsibility with a professional who fulfills the conditions provided for under Sub-article (3) of this Article and performs its duties in a manner consistent with these conditions following the delegation.

www.chilot.me

https://chilot.me



**፴፯. የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት**

፩/ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው የሥልጣንና ተግባር ማእቀፍ ውስጥ የሽብር ወንጀልን ይከታተላል፤ ለዚህ አላማ የመሥሪያ ቤቱን ሠራተኞችን መርጦ ይመድባል፤ የተለየ የሥራ ክፍልም ያደራጃል፡፡

፪/ የሽብር ጉዳይን ለመከታተል የሚመድበው ባለሙያ በሽብር ጉዳይ እና በሰብአዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ስልጠና የወሰደ፣ መልካም ስነ-ምግባር፣ የሥራ ልምድ እና ክህሎት ያለው መሆን አለበት፡፡

፫/ በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ወይም የአገልግሎቱ ሠራተኛ በሽብር ወንጀል የተጠረጠረን ሰው ለማሰር አይችልም፤ ሆኖም የሽብር ወንጀልን ሊፈጽም ያለን፣ እየፈጸመ ወይም ፈጽሞ ያለን ሰው ለመያዝ የሚችል ሲሆን በአቅራቢ ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ለማስረከብ ህጉ በሚጠይቀው ጊዜ ውስጥ ለፖሊስ የማስረከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

**፴፰. የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፦

ሀ) በሽብር ወንጀል የሚደረግን ምርመራ ይመራል፤ በፍርድ ቤት ክርክር ያደርጋል፤

ለ) በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ወንጀል ምርመራ የሚመራና ክርክር የሚያደርግ ባለሙያ የተለየ የሥራ ክፍልም ያደራጃል፤

ሐ) በሽብር ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው አያያዝ በህግ መሰረት መሆኑን ይከታተላል፤

፪/ በሽብር ወንጀል በምርመራ የሚሳተፍ እና የፍርድ ቤት ክርክር ለማድረግ የሚመደበው ባለሙያ በሽብር ጉዳይ እና በሰብአዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ስልጠና የወሰደ፣ የሥራ ልምድ፣ ክህሎት እና መልካም ስነ-ምግባር ያለው መሆን አለበት፡፡

**37. National Intelligence and Security Service**

1/ The National Intelligence and Security Services shall follow up Terrorism Crime within the scope of Power and Functions given under its establishment Proclamation and shall recruit and assign from among its employees for this purpose. where necessary, organize a special work unit.

2/ A professional to be assigned to follow up on case of terrorism shall be a person who has taken training on matters of crimes of terrorism and protection of Human Rights and who possesses the required experience, skill and good ethical behavior.

3/ The National Intelligence and Security Service or its officer shall not detain a person suspected of terrorism crime. Provided however, may arrest a person who is about to commit or is in the act of committing or has committed a terrorism crime and shall have the responsibility to handover to a police officer immediately.

**38. Federal Attorney General**

1/ The Federal Attorney General shall:

a) Lead the investigation of terrorism crime and conduct litigation in a court of law;

b) Assign a professional who leads the investigation and conduct litigation and, where necessary, set up a special work unit;

c) Follow up the treatment of detainee suspected of committing crime is in compliance with the law;

2/ A professional who has taken training on matters of crimes of terrorism and protection of Human Rights and who possesses the required experience, skill and good ethical behavior shall be assigned to participate in the investigation of terrorism crime and conduct litigation.

www.chilot.me

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለክልል ዓቃቤ ህግ ተቋም በውክልና ሲሰጥ ውክልና የሚሰጠው የክልል ዐቃቤ ህግ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ሁኔታ በሚያሟላ ባለሙያ ኃላፊነቱን ሊወጣ የሚችል እንዲሁም ውክልናው ከተሰጠው በኋላም ሁኔታውን ባሟላ መልኩ እየፈጸመ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

## ፴፱. <u>የዳኝነት ሥልጣን</u>

፩/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጊዜ ቀጥሮ፣ የመያዣ እና የብርበራ ትዕዛዝ መስጠትን ጨምሮ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮችን (ክሶችን)፤

ለ) በዚህ አዋጅ ከተመለከቱ ወንጀሎች ጋር ተያይዘዉ የሚፈፀሙ ሌሎች ወንጀሎችን፤ ወይም

ሐ) በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረቡ ክሶችና ፍርድ ቤቱ አንቀጽ የቀየራቸውን ጉዳዮችን፤የመዳኘት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የመያዣ ወይም የብርበራ ትዕዛዝ የሚያስፈልግ ሆኖ ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እስከሚወጣ ተጠርጣሪ ሊሰወር የሚችል ወይም ማስረጃው ሊጠፋ የሚችል ሲሆን የመያዣ ወይም የብርበራ ትዕዛዝ የወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ሥልጣን ያለው ማንኛውም ፍርድ ቤት ለመስጠት ይችላል፡፡

፫/ ፍርድ ቤቶች በሽብር ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘው ወይም የተከሰሰው ሰው ከአያያዙ ጋር በተያያዘ በሚያነሳው የመብት ጥያቄ ቅድሚያ በመስጠት መመርመር እና ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ መስጠት አለባቸው፡፡

3/ Where the Federal Attorney General delegates his Powers entrusted under this Proclamation to regional prosecution institution, it shall have the obligation to ensure that the regional public prosecution Institution carries out its responsibility with a professional who fulfills the conditions provided for under Sub-article (2) of this Article and performs its duties in a manner consistent with the conditions following the delegation.

## 39. <u>Jurisdiction</u>

1/ The Federal High Courts and the Regional Supreme Courts shall, in addition to granting of remand, issuing of warrant of arrest and search warrant, have jurisdiction over:

a) Cases presented before it in accordance with this Proclamation;

b) Other crimes committed in connection with crimes provided for under this Proclamation; or

c) Cases presented before it in accordance with this Proclamation and the court changes the article of the charge.

2/ Notwithstanding Sub-article (1) of this Article, in case where having warrant is necessary, any court may issue warrant of arrest or search warrant where the suspect is likely to abscond or the evidence is likely to be removed until a warrant is issued Federal High Court or the Regional Supreme Court.

3/ The Courts shall give priority to claims raised in relation to detention by a person detained on suspicion of committing a terrorism crime or tried in court of law and investigate and issue the appropriate order for correction.

፬/ የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተ የወንጀል ህግ አንቀጽ ፲፫ እና ፲፯(፩) (ለ) ድንጋጌዎች የሽብር ወንጀሎችንም ያካትታሉ፡፡

**፵. ስለብሔራዊ የሽብር ወንጀል መከላከል አስተባባሪ ኮሚቴ**

፩/ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር የሽብር ድርጊትን ለመከላከል አግባብነት ያላቸውን ተቋማት ያቀፈ የብሔራዊ የሽብር ወንጀል መከላከል አስተባባሪ ኮሚቴ ያዋቅራል፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የኮሚቴውን ይመራል፡፡

፪/ የሽብር ወንጀል መከላከል አስተባባሪ ኮሚቴው የጋራ የሽብር መከላከል ዕቅድ ያወጣል፣ የጋራ የሽብር መከላከል ግብረ ኃይል በማደራጀት ተቋሞቹ ሽብርን ለመከላከል የሚያደርጉትን ጥረት በማቀናጀት በጋራና በተደጋጋፊነት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ህጎች ለየተቋማቱ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራትን አንዱ ተቋም ለሌላኛው ተቋማት አሳልፎ መስጠት ወይም ጣልቃ መግባትን የሚፈቀድ መሆን የለበትም፡፡

**፵፩. የአስፈጻሚ አካላት ተጠያቂነት**

፩/ በዚህ አዋጅ የተመለከተ ወንጀልን የመከላከል፣ የመመርመር ወይም የክርክር ሂደትን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም ሰው የተሰጠውን ኃላፊነት ህግን በመተላለፍ የፈጸመ እንደሆነ እንደመተላለፉ ዓይነት እና እንዳስከተለው ጉዳት ዓይነት በዲስፕሊን፣ በፍትሐብሔር እና በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ይህንን አዋጅ የሚያስፈጽሙ ሰዎች የህግ ጥሰት የፈጸሙ እንደሆነ ተጠያቂ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

4/ The provisions of Article 13 and Sub-article (1) (b) of Article 17 of the Criminal Code concerning jurisdiction shall includes terrorism crimes.

**40. National Anti-Terrorism Coordinating Committee**

1/ The Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall set up a National Anti-Terrorism Coordinating Committee comprising of the relevant institutions in order to prevent terrorist acts, The National intelegence and security service shall lead the Committee.

2/ The Committee shall prepare a joint anti-terrorism plan and organize a joint anti-terrorism task force by coordinating the efforts that are being undertaken and cause to work in a coordinated and interdependent manner.

3/ The implementation of this Article shall not permit the relinquishing of the Powers and Duties of one institution to the other or interference of one in the other.

**41. Accountability of Executive Organs**

1/ Any person entrusted with the responsibility of preventing and investigating crimes or conducting litigation concerning crimes provided for in this Proclamation shall, depending on the types of violation and the damage caused as a result of the violation, be subject to disciplinary action or be held civilly and criminally liable.

2/ The Federal Attorney General shall have the duty to ensure that persons who carry out the duties provided in this Proclamation shall be accountable if they are found in violation of the law.

፫/ ፍርድ ቤት በወንጀል ክርክር ሂደቱ የህግ አስፈጻሚ አካላት የህግ ጥሰት የፈጸሙ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ የወንጀሉ ጉዳይ እንዲጣራ ትእዛዝ መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላ ህግ የበለጠ የሚያስጠይቅ ካልሆነ በስተቀር ጥሰት የፈጸመው ሰው ወይም ተቋም ለተጎጂው ከአስር ሺህ ብር እስከ መቶ ሺህ ብር የሚደርስ የህሊና ጉዳት ካሣ እንዲከፍል በያዘው የክርክር መዝገብ ለመወሰን ይችላል፡፡

፬/ ተጎጂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት ከተወሰነለት የህሊና ጉዳት ካሣ ውጭ ያለን የጉዳት ካሣ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ የምርመራ ዘዴዎችና ስለመጠቀምና መረጃ የመስጠት ግዴታ

### ፵፪. ልዩ የምርመራ ዘዴን ስለመጠቀም

፩/ በሀገር እና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል የሚል ሽብር ወንጀል ስጋት ሲኖር ፖሊስ በመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት ማስረጃ ማሰባሰብ ሳይቻለው ሲቀር የሚከተሉትን ልዩ የምርመራ ዘዴዎች በመጠቀም ማስረጃ ለመሰብሰብ ይችላል፡፡

ሀ) ተጠርጣሪው በፖስታ፣ በደብዳቤ፣ በቴሌፎን፣ በፋክስ፣ በራድዮ፣ በኢንተርኔት እና በሌሎች የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸውን ልውውጦች ወይም ግንኙነቶች በመመርመር ወይም በመጥለፍ፤

ለ) ክትትል በማድረግ ወይም ድምጽ ወይም ፎቶግራፍ ወይም ተንቀሳቃሽ ምስል መቅረጽ የሚያስችል መሣሪያ በመጠቀም፤

ሐ) ሠርጎ በመግባትና አብሮ በመሆን የተጠርጣሪዎችን እንቅስቃሴና ድርጊት በመከታተል፤

መ) የይምሰል ግንኙነቶችን በመፍጠር፡፡

3/ Where during the proceedings, the court finds that the Executive Organ performed in violation of the law, it may on the same file, orders the person or the institution that violated the law to compensate the victim a moral damages from Birr ten thousand to hundered thousand birr.

4/ The victim may claim compensation for damage other than the moral damage awarded pursuant to Sub-article (3) of this Article.

## Section Six

## Special Investigation Techniques Employment and Duty to Provide Information

### 42. Special Investigation Techniques Employment

1/ Police may use the following special investigation techniques if an act of terorrorism has a serious damage to the country and public, where in the regular Criminal Procedure Code investigation technique is not effective to gather evidence regarding investigation of terrorism crime.

a) Intercepting or conducting surveillance on postal, letter, telephone, fax, radio, internet and other electronic devices exchange or communications of a person suspected of terrorism.

b) Conducting surveillance or installing camera, audio or video recording devices.

c) Infiltrating and collaborating the suspect’s group and follow up their activities.

d) Creating simulated communication.

፪/ ፖሊስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገጉ ልዩ የማስረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚችለው ፍርድ ቤት የምርመራውን አስፈላጊነት አምኖ ሲፈቅድ ብቻ ነው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ፖሊስ አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመው በአካባቢው ያለውንና የሚመለከተውን የዓቃቤ ህግ ተቋም ኃላፊ በማስፈቀድ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ሊሰበስብ ይችላል፡፡ ሆኖም ፖሊስ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ለመሰብሰብ በጀመረ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ምክንያቶቹንና በዐቃቤ ህግ የተሰጠውን ጊዚያዊ ፈቃድ ጨምሮ ለፍርድ ቤት በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ፍርድ ቤቱም የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል፡፡ በተሰጠው ትእዛዝ ላይም ይግባኝ አይቀርብበትም፡፡

፬/ ፍርድ ቤት በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበስብ ለፖሊስ ፈቃድ ሲሰጥ፡-

ሀ) ማስረጃ ስለሚሰበሰብበት ዘዴ እና ስለሚከናወንበት አግባብ፤

ለ) የሚከናወንበት ጊዜ፤

ሐ) የማስረጃ ማሰባሰቢያው ዘዴ ጠለፋ ወይም ክትትል እንደሆነ ጠለፋዉ ወይም ክትትሉ የሚደረግበትን የስልክ፤ የፋክስ፤ የሬዲዮ፤ የኢንተርኔት፤ የኤሌክትሮኒክስ፤ የፖስታና የመሳሰሉትን የግንኙነት መስመሮች አድራሻ ወይም መለያ፤መጥቀስ አለበት፡፡

2/ Special investigation technique stipulated under Sub article 1 of this Article may only be employed on the authorization of the court where the court believes the necessity of the use of special investigation techniques.

3/ Notwithstanding to the provision of sub-article (2) of this Article, for urgent conditions police may gather evidences through special investigation techniques without the authorization of the court with the permission of the head of the nearest and appropriate public prosecutor institution. However, police shall provide the temporary permission obtained from the public prosecutor institution and his good cause in writing to the court within 48 hours. The court also may accept or deny the petition after investigating its relevancy. There shall be no appeal to the order of the court.

4/ When the Court authorizes the use of special investigation technique, the order of the Court shall include:

a) Techniques how the evidence sought to be collected, and perform;

b) The time period within which the authorization shall be executed;

c) Techniques of gathering evidences whether it is interception or surveillance should mention address's of telephone, fax, radio, internet, electronics, postal or others similar communication lines or identifications applied in the interception or surveillance.

፭/ ማንኛውም የመገናኛ አገልግሎት አቅራቢ በፖሊስ ጠለፋውን ለማካሔድ ሲጠየቅ ጠለፋው በፍርድ ቤት የተፈቀደ መሆኑን በማረጋገጥ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

፮/ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በሕግ አስከባሪ አካላት በጠለፋ የተገኙ ማስረጃዎች በጠለፋ በተገኙበት መልክ በቀጥታ ካልቀረቡ በቀር ዋጋ አይኖራቸዉም፡፡

፯/ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ መሰረት በልዩ የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ለማሰባሰብ የሚፈቅደው ጊዜ ከ፺ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡ ፖሊስ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ የሚፈለገውን ማስረጃ ያላገኘ እና ልዩ የምርመራውን ዘዴ መጠቀሙ ተጨማሪ ጊዜ አስፈላጊ ለመሆኑ በቂ ምክንያት ያለው ከሆነ ፍርድ ቤቱን ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም ፖሊስ ያከናወነውን ተግባር፣ የተፈቀደው ዘዴ እያስገኘ ያለውን ውጤት በማገናዘብ እና ተጨማሪ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን በመመርመር ከ፴ ቀናት ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ልዩ የምርመራ ዘዴ ለማከናወን የሚቀርብ ጥያቄ፣ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ፈቃድ በልዩ የምርመራ ዘዴ እና በልዩ የምርመራ ዘዴው የተገኙ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማስረጃ የማሰባሰቡ ሁኔታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በፖሊስ፣ በዓቃቤ ህግ፣ በፍርድ ቤት እና መረጃው የደረሳቸው ሌሎች አካላት በሚስጥር መያዝ አለበት፡፡ ማስረጃ ማሰባሰቡ ከተጠናቀቀ በኋላም ለማስረጃነት የሚያገለግሉ ካልሆነ በስተቀር በልዩ የምርመራ ዘዴው የተገኙት መረጃዎች መወገድ አለባቸው፡፡

5/ Any communication service provider shall cooperate when it is requested by the police to conduct the interception by ensuring the court's authorization order.

6/ Evidences obtained through interception by national or foreign law enforcement organs shall not be valid where they are not presented directly as they are obtained.

7/ The special investigation authorization granted by the court in accordance with this Article shall not exceed 90 days. Where the police officer petitions the court for an extension of the time, the court may for good cause extend its authorization of using special investigation technique. The court may give extension by investigating the performance of the police and evaluating the significance of using special investigation technique for not more than 30 days.

8/ In accordance with this Article, petition of special investigation technique, the authorization granted by the court, evidences and information obtained through special investigation shall be kept in secret by police, public prosecutor, court and other organs which have obtained the information until the conditions completed. Where the evidence collected through the special investigation technique is not relevant as an evidence, it shall be destroyed.

፵፫. **መረጃ የመስጠት ግዴታ**

፩/ ማንኛውም ሰው ከአቅም በላይ በሆነ እና አደጋ የማያስከትልበት ከልሆነ በስተቀር ፖሊስ የሽብር ወንጀልን ለመከላከል ወይም ምርመራ ለማከናወን የሚረዳዉ መሆኑን በሚገባ የሚያምንበትን መረጃ ወይም ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም መረጃው ወይም ማስረጃው የተጠርጣሪውን የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብትን የሚጎዳ ከሆነ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ እንዲሰጠዉ ለመጠየቅና ለመውሰድ ይችላል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ፖሊስ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥመው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መረጃውን ወይም ማስረጃውን ለመጠየቅና ለመውሰድ ይችላል፣ ሆኖም ጉዳዩን በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ለፍርድ ቤት የማሳወቅና ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ትዕዛዝ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

፬) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) መሰረት የተገኘው መረጃ ወይም ማስረጃ ሚስጥራዊ ይዘት ያለው እንደሆነ፣ ፖሊስ መረጃውን ወይም ማስረጃውን በሚስጥር የመያዝ እና ለተፈለገበት ዓላማ ብቻ የማዋል ግዴታ አለበት፡፡

43. **Duty to Provide Information**

1/ Any person who has information or evidence which assists police to prevent terrorist attack or investigation shall have the duty to provide information or evidence if it is not beyond his capacity and does not cause danger.

2/ Notwithstanding to the provision of Sub-article (1) of this Article, when the information or evidence requested defamatory to protection of the suspect's rights to privacy police may request and collect such evidence or information from any Government Iinstitution, private organization or an individual by the court order.

3/ Notwithstanding to the provision of Sub-article (2) of this Article, when police come across urgency shall request and take the information or evidences without court order. However, police shall notify to the court within seventy two hours and also has duty to respect the court's order.

4/ In accordance with Sub-article (2) or (3) of this Article, when information or evidence obtained has a content of secrecy, police shall have duty to keep the information and evidences in secret and apply only for the targeted objectives.

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፵፬. ፈንድ ስለማቋቋም

፩/ የሽብር ወንጀል ተጎጂዎች ፈንድ (ከዚህ በኋላ ፈንድ እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የሚቋቋመው ፈንድ ዓላማ፡-

ሀ) የሽብር ወንጀል መከላከል አገልግሎት፣

ለ) በሽብር ጥቃት ጉዳት የደረሰባቸውን ተጎጂዎች የህክምና ወጭ መሸፈን፣

ሐ) በሽብር ጥቃት ጉዳት የደረሰባቸውን ተጎጂዎች እንደአግባብነቱ መልሶ ማቋቋም፣ እና

መ) የሽብር አስተሳሰብ እንዲሰርጽባቸው የተደረጉ ሰዎችን የተሐድሶ አገልግሎት፣ ድጋፍ ማድረግ

፫/ የፈንዱ የገቢ ምንጭ የፈንዱን አስተዳደር ለመወሰን በሚወጣው ደንብ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል ምክንያት የሚወረስ ንብረት እና በፍርድ ቤት የሚወሰን መቀጮ ለፈንዱ ገቢ ይደረጋል፡፡

፬/ ስለፈንዱ አስተዳደር፣ የገቢ ምንጭ፣ ለተጎጂዎች አገልግሎት ስለሚውልበት፣ እና ተያያዥ ጉዳዮች ስለሚፈጸሙበት አግባብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## PART SEVEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 44. Establishment of Fund

1/ A terrorism crimes victims fund (here in after referred as the fund) is hereby established.

2/ The objective of the fund shall be to provide support for:

a) Prevention of terrorism crimes;

b) Covering medical expenses of victims of terrorist acts;

c) Rehabilitation of victims of terrorist acts as may be appropriate; and

d) Rehabilitating persons in whom terrorist ideas are inculcated.

3/ Without prejudice to the source of funding provided for in the Regulation to be issued by the Council of Ministers, the confiscated property and fine imposed by a court of law in criminal proceedings in connection with this Proclamation shall be credited to the fund.

4/ The Council of Ministers shall issue Regulation regarding administration, income, manner of use for victims, and other related matters of the fund.

www.chilot.me

**፵፭. <u>የተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በማቆያ ወይም በማረሚያ ቤት የአያያዝ ሁኔታ</u>**

በዚህ አዋጅ በተመለከተ ወንጀል ተጠርጥሮ ወይም ተከሶ በማቆያ ቤት ወይም በማረሚያ ቤት ያለ ሠው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፣ ኢትዮጵያ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የአገሪቱ ህጎች ስለተጠረጠሩ እና ስለተከሰሱ ሰዎች የተቀመጡ መብቶችና ሁኔታዎች መጠበቅ አለበት፡፡

**፵፮ <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ.፩ በዚህ አዋጅ የተጀመሩ የሽብር ጉዳይን በተመለከተ ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች፣ ይህ አዋጅ ለተከሳሽ የተሻለ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ.፩ መሰረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

**፵፯ <u>ስለማይሸፈኑ ጉዳዮች</u>**

፩/ የጦርነት ህግን የሚመለከተው የጄኔቫ ኮንቬንሽን እና ፕሮቶኮሎቹ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ጉዳዮች ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ በአሸባሪነት በተሰየመ ድርጅት ላይ ወይም በዚህ አዋጅ በአሸባሪነት ከተሰየመ ድርጅት ጋር በተያያዘ በሚፈፀም የሽብር ወንጀል ላይ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ነው፡

**45.<u>Treatment of Suspect or Accused in Detention or Prison</u>**

A person who is in detention center or prison on suspicion or accusation in connection with crimes provided for in this Proclamation shall be protected in accordance with the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia, International Agreements ratified by Ethiopia and other Laws of the country concerning Rights and conditions of suspected or accused persons.

**46. <u>Transitional Provision</u>**

Unless this Proclamation favors the accused person, all pending cases before the coming in to force of this Proclamation shall continue to be governed in accordance with the Anti-Terrorism Proclamation No. 652/2009.

**47. <u>Matters Excluded</u>**

1/ This Proclamation is not applicable to matters covered by the Geneva Convention and Protocols thereof.

2/ Notwistanding the provisions of sub Article 1 of this Article Terrorism Crime commited Organization proscribed by terrorist act this Proclamation shall be applicable.

www.chilot.me

**፵፰. ስለተሻረ ህግ እና ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ድንጋጌዎች**

፩/ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ የወንጀል ህግ በዚህ አዋጅ በግልጽ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ ልዩ የምርመራ ዘዴን ስለመጠቀምን አስመልክቶ በአንቀጽ ፵፪ ላይ የተደነገገው ድንጋጌ ጸንቶ የሚቆየው የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህጉ ጸድቆ ተግባራዊ እስከሚሆንበት ዕለት ድረስ ብቻ ነው።

**፵፱ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ሣህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**48. Repealed Law and Inapplicable Provisions**

1/ Anti-Terrorism Proclamation No. 652/2009 is hereby repealed.

2/ Issues clearly covered hereby this proclamation shall not applicable under criminal law.

3/ Notwistanding to this proclamation under Article 42 this proclamation on special investigation techniques shall be enforce until Criminal Law Procedure and Evidence Law take to effect .

**49. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**DONE AT ADDIS ABABA, ON THE 25TH DAY OF MARCH, 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me